# እንግዶች እንኳን ደህና መጣችሁ!

## ማስታወቂያ

### የአርብ ፕሮግራም

ዘወተር አርብ በሚኖረን የጸሎትና የቃል ፕሮግራም ላይ በመገኘት እንድንካፈል ቤተ ክርስቲያን ታበረታታለች። በዚህ ፕሮግራም ላይ ቃሉን እንማራለን፣ በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ እንጸልያለን። በተለይም ደግሞ በዚህ ሰሞን ስለ አግራችን ኢትዮጲያ ጸልትና ምልጃ በጥብቅ የምናደርግበት ስለሆነ ተግኝተን እንድንተጋ ቤተ ክርስቲያን ታሳስባለች። ጌታ ይባርካችሁ!

### አገልግሎት

የድምጽና የምዚቃ መሳሪያዎችን በማስተካከል ለማገልገል የምትፈልጉ ዔሊያስን ወይንም ሽማግሌዎችን እንድታነጋግሩ እንጠይቃለን። በሌሎች አገልግሎቶችም ለማገልገል የምትፈልጉ ሽማግሌዎችን እንድታነጋግሩ እናበራታታለን።

"ወደ ውጭም አውጥቶ፡- ጌቶች ሆይ፥ እድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል? ኣላቸው።
እነርሱም፡- በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተና ቤተ ሰዎችህ ትድናላችሁ አሉት።" (ሐዋ. 16፡ 30-31)



- ⇒ የእሁድ ፕሮግራም ይካፈላሉ?
- ⇒ የአርብ ፕሮግራም ይካፈላሉ?
- ⇒ በምጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ይካፈላሉ?
- ⇒ ማገልገል ይፈልጋሉ?
- ⇒ Yeec.org App ጭነዋል?
- ⇒ http://www.yeec.org/ ይጎበኛሉ?


ሽማግሌዎችን ለማግኘት፡-
773-886-0818 (ወ/ም ሲሳይ)
773-507-0194 (ወ/ም አያሌው)
773-910-0485 (ወ/ም ፒተር)
773-961-5332 (ወ/ም ጌቱ)
773-739-0437 (ወ/ም ሰለሞን)


### መደበኛ ፕሮግራሞች

እሑድ 1፡30 p.m. -- 4፡30 p.m.
አርብ 7፡00 p.m. -- 9፡00 p.m.

# የቺካጎ የምስራች ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን

# Chicago Yemsrach Evangelical Church

"እነሆ፥ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ" ሉቃስ 2፡10




*"አንተ ግን እስከ ፍጻሜው ድረስ ሂድ፤ አንተም ታርፋለህ፥ በቀኑም መጨረሻ በዕጣ ክፍልህ ትቆማለህ።" (ዳን. 12:13)*


Chicago Yemsrach Evangelical Church
4455 N. Seeley Avenue
Chicago, IL 60625


www.yeec.org

መደበኛ ፕሮግራሞች


እሑድ 1፡30 p.m. -- 4፡30 p.m.
አርብ 7፡00 p.m. -- 9፡00 p.m.


**February 25, 2018** | **የካቲት 18፣ 2010 ዓ.ም.**

## የእለቱ አገልግሎት መርሃ-ግብር

ጸሎት መሪ................. እህት ሰናይት ከበደ

አምልኮ....................... የቤተክርስቲያን አምልኮ ቡድን

ፕሮግራም መሪ .......... ወንድም አያሌው አስፋው

ቃል ............. ወንድም ሰለሞን ወመጎ

ማጠቃለያ ................. ፕሮግራም መሪ

### <u>የሳምንቱ ጥቅስ</u>

“ገንዘብን መውደድ የክፋት ሁሉ ሥር ነውና፥ አንዳንዶች ይህን ሲመኙ፥ ከሃይማኖት ተሳስተው በብዙ ሥቃይ ራሳቸውን ወጉ።

አንተ ግን፥ የእግዚአብሔር ሰው ሆይ፥ ከዚህ ሽሽ፤ ጽድቅንና እግዚአብሔርን መምሰል እምነትንም ፍቅርንም መጽናትንም የዋህነትንም ተከታተል።”

(1 ጢሞ 6፡ 10-11)

**የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድኖች**

| መሪ | ቀን | አድራሻ |
|---|---|---|
| ወ/ም አያሌው አስፋው | ማክሰኞ | 5030 N. Marine Dr., Chicago, IL 60640 |
| እህት ሰናይት ከበደ | ማክሰኞ | 7200 N. Ridge Ave., Chicago IL 60660 |
| ዶ/ር ተረፈ አንሼቦ | ማክሰኞ | 7526 N. Ridge Blvd., Unit #3W, Chicago IL 60645 |
| ወ/ም ረድኤቱ ካሳ | ሐሙስ | 7252 W. Everell Ave., Chicago, IL 60631 |
| ወ/ም ሳሚ ኃብተየስ | ሰኞ | 9107 Laramie St. Skokie, IL 60077 |
| ወ/ም ዮናስ ባህሩ | ማክሰኞ | 5523 N. Kenmore Ave., Chicago, IL 60640 |
| ወ/ም ሰለሞን ወመጎ | ቅዳሜ | 549 Sheridan Rd., Apt. 3, Evanston, IL 60202 |

## መልዕክተ ሰንበት

ወ/ም ረድኤቱ ካሳ

### ወንጌላዊ ቢሊ ግራሃም -- የወንጌል አርበኛ

*“መልካሙን ገድል ተጋድዬአለሁ፥ ሩጫውን ጨርሼአለሁ፥ ሃይማኖትን ጠብቄአለሁ፤ ወደ ፊት የጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶልኛል፥ ይህንም ጻድቅ ፈራጅ የሆነው ጌታ ያን ቀን ለእኔ ያስረክባል፥ ደግሞም መገለጡን ለሚወዱት ሁሉ እንጂ ለእኔ ብቻ አይደለም።” (2 ጢሞ 4፡ 7-8)*

ሰሞኑን በመገናኛ ብዙሃን እንደሰማነው ታዋቂው የወንጌል አርበኛ ወንጌላዊ ቢሊ ግራሃም በ99 አመታቸው የምድር አገልግሎታቸውን ጨርሰው ወደ ሚወዳቸውና ወደ ሚወዱትና ጌታ በፌቡራሪ 21፣ 2018 በክብር ሄደዋል። ዜና እረፍታቸውን ተከትሎ በበርካታ የመገናኛ አውታሮች ሕይወታቸውና አገልግሎታቸው ሲዘከር ሰንብቷል። እኛም በዛሬው የሰንበት መልክታችን እኚህን ታላቅ የወንጌል ሰው በጥቂቱ እናስታውሳለን።

በ16 አመታቸው ጌታን የተቀበሉት ወንጌላዊ ግርሃም ዘመናቸውን ሁሉ ጌታን በማገልገል ፈጽመዋል። አዘውትረው ከዮሐንስ 3:16 በመነሳት ወንጌል የሚሰብኩት ወንጌላዊ ግራሃም በክርስቶስ የተገለጠውን የእግዚአብሔር ፍቅር በመስበክ ይታወቃሉ። ወንጌላዊ ግራሃም በ185 አገሮች ተጉዘው ለ215 ሚልዮን ሰዎች የምስራቹን ወንጌል ሰብከዋል። ከዚህ መካከል በአግራችን በ1960 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ላይ ያደረጉት ክሩሴድ አንዱ ነው። ከዚህም በተጨማሪ ብዙ ሚሊዮን ሰዎችን በጽሑፍ፣ በቴሌቪዥን፣ በሬዲዮ፣ በፊልም፣ በፊዲዮና በኢንተርኔት በወንጌል ደርሰዋል። በዚህ አገልግሎታቸው ከ2.6 ሚሊዮን በላይ ሰዎች ለወንጌሉ ጥሪ ምላሽ እንደ ሰጡ መረጃዎች ያሳያሉ። እኚህ የ20ኛው ክፍለ ዘመን ታላቅ የወንጌል ሰው እስከዛሬም ድረስ በተቀረጹ ስብከቶቻቸው ጌታን ለትውልዱ እየሰበኩ ይገኛሉ።

የወንጌላዊ ግራሃም የወንጌል ተጽእኖ በቤተ ክርስቲያን ክልል ብቻ የተወሰነ አልነበረም። የአሜሪካ ፕሬዚዳንቶች መንፈሳዊ አማካሪ የሆኑት ወንጌላዊ ግራሃም ከፕሬዚዳንት ሄሪ ቱርማን እስከ ፕሬዚዳንት ባራክ ኦባማ ድረስ ያሉትን ፕሬዚዳንቶች አማክረዋል። በአገልግሎታቸው የዘር ክፍፍልንና የዘር መድሎን በጽኑ ተቃውመዋል። ኮሚኒዝምንምና የተመሳሳይ ጾታ ጋብቻን በማውገዝም ይታወቃሉ። ሰላሳ ሶስት መጻህፍትንም በመጻፍ ትውልዱን በእውቀት አንጸዋል።

ወንጌላዊ ግራሃም የሚታወቁት አስደናቂ በሆነው አገልግሎታቸው ብቻ ሳይሆን በኖሩትም ጌታን ያስከበረ የተቀደሰ ህይወት ጭምር ነው። በዊተን ኮሌጅ ተዋውቀው ከታጋቡት የትዳዳር አጋራቸው ከሩት ግራሃም ጋር ሞት እስኪለያቸው ድረስ ለ64 አመት በጸናና ጌታን ባስከበረ ትዳር ኖረዋል። ቢሊ ግራሃም ገንዘብ፣ ዝና፣ አለም ያልበግራቸው የጽድቅ አገልጋይ ነበሩ። የቢሊ ግራሃም የህይወታቸው አንደኛ አላማ ሰዎች በክርስቶስ በማመን ከእግዚአብሔር ጋር የግል ግንኙነት እንዲኖራቸው መርዳት ነበር። እኚህ ትሁት የእግዚአብሔር ሰው የአገራቸውን ለሲቪል ሰዎች የሚሰጠውን የመጨረሻ ሽልማት (Presidential Medal of Freedom) ጨምሮ በርካታ ሽልማቶችና ምስጋናዎችን ተቀብለዋል። የመጨረሻውን የሕይወት አክሊል ሽልማት ደግሞ ከጌታቸው ለመቀበል ወደ ቤታቸው ሄደዋል -- የወንጌል አርበኛው ቢሊ ግራሃም።